**ኤፒኤችአይኤስ** **ፋክትሺት**

*የተክሎች መንከባከቢያና መቆጣጠሪያ* ነሃሴ 2012

# ምግብ እና ግብርና ነክ ምርቶችን ወደአሜሪካ ማስገባት

በአለም ላይ ተንሰራፍተዉ የሚገኙ ግብርናን የሚያጠቁ ነፍሳትና የበሽታ አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል፤ ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ወደአሜሪካን አገር በተለያዩ ከዉጪ አገር በሚመጡ እቃዎች (ለምሳሌ ያህል በስጋ በእንስሳትና በእንስሳት ተዋፅኦ በፍራፍሬና በአትክልት በሌሎች ተክሎች በአፈርና ተክሎች ዘርና የተክሎች ዉጤቶች በሆኑ የእጅ ስራዎች) ሊገቡ እንደሚችሉ ይገመታል።በነዚህ ስጋቶች የተነሳ የአሜሪካ እንስሳት ግብርና ክፍል (USDA) ከተክሎች ጤና አጠባበቅ አገልግሎት (APHIS) ጋር በመተባበር ከዉጪ ወደአሜሪካ በሚገቡ አንዳንድ የግብርና ዉጤቶች ላይ ቁጥጥር ያደርጋል።

እንደነዚህ አይነት የግብርና አቅርቦቶችን ከማስገባትህ በፊት አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ቅድመ ሁኔታዎችንና መመዘኛ ስርአቶችን መገንዘብ ይኖርብሃል፡ ፡እነዚህን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ማወቅህ አላስፈላጊ ከሆኑ ወጪዎች ቅጣቶችና ግራ መጋባት ይጠብቁሃል።

## አጠቃላይ መረጃዎች

በአሜሪካ የአገር ዉስጥ ፀጥታና የድንበር ጥበቃ ክፍል (CBP) በዋነኛነት የ APHISን ህጎች በወደቦችና ድንበር አካባቢዎች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸዉ ያደርጋል።የCBP ግብርና እስፔሻሊስቶች ከዉጪ የሚመጡ ዉጤቶችን በመፈተሽና በማረጋገጥ የሳኒተሪ ቁጥጥር ሰርተፍኬት (ለእንስሳት ዉጤቶች) እንዲሁም የፎቶሳኒተሪ ሰርተፍኬት (ለተክሎች ቁጥጥር) መስፈርቶች ማለፋቸዉንና በያንዳንዱ ዐቅርቦት ላይ በትክክል መኖሩን ያረጋግጣሉ።

ሳኒተሪና ፎቶሳኒተሪ ሰርተፍኬት ከላኪዉ ሀገር የሚላኩ ህጋዊ መረጃዎች ሲሆኑ ጥቅማቸዉም የተላኩት አቃዎች ያሜሪካንን የእንስሳትና እፅዋት የቁጥጥር መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያሙዋሉ መሆናቸዉን ይገልፃል።ለምሳሌ ያህል ፎቶሳኒታሪ ሰርተፍኬት ወደዉስጥ በተላኩት ዕቃዎች ላይ አስፈላጊ የሆነ ማጠንት እንደተከናወነና እያንዳንዱ አቅርቦት በቅድመሁኔታ ምርመራ አልፎ ከ ተባይና ከሌሎች ተያያዥ በሽታዎች የፀዳ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሁሉም አስመጪ ድርጅቶች ማወቅ ያለባቸዉ APHIS ከእፅዋትና ከ እንስሳት አቅርቦቶች በተጨማሪ የእፅዋትና እንስሳት ዉጤቶችን በዋነኛነት ይቆጣጠራል፤ለምሳሌ ያህል ለዐዝዕርት የሚያገለግሉና ለውበት ዕቃዎች ማስጌጫ የሚሆኑ ዘሮችን ይቆጣጠራል።እነዚህን ለንግድ የተዘጋጁና የታሸጉ የግብርና ዉጤቶችን ወደአሜሪካን ሃገር በህጋዊ መንገድ ለማስገባት ትክክለኛ የሆነ ፈቃድ ወይም መረጃ እንዲሁም የሚገቡት አቃዎች የአሜሪካንን የእፅዋትና እንስሳት የጥራት መስፈርቶች ያሙዋሉ መሆናቸዉን ከላኪዉ አገር መስረጃ መላክ ይኖርባቸዋል።ከዚህም በተጨማሪ አስመጪዎች ሊገነዘቡት የሚያስፈልገዉ ነገር ከአንዳንድ አገሮችና አህጉራት የሚገቡ እቃዎች ካለዉ የቦታዉ በተደጋጋሚ በታየ የተባዩችና የበሽታዎች መንሰራፋት ምክንያት ወደአሜሪካን ሃገር እንዳይገቡ ተከልክለዋል።

## ዕፅዋትና የእፅዋት ዉጤቶች

ዕፅዋትና የእፅዋት ዉጤቶች ወደሃገር ዉስጥ ሊገቡ የሚችሉ ግብአቶችን ለማግኘት ካሻዎ በAPHIS የአትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት መስፈርቶች መረጃ ማእከል (FAVIR) ወይም በድክረገፁ www.aphis.usda.gov/favir/ በመግባት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።የመረጃ አገልግሎቱ ደንበኞች የአትክልትና ፍራፍሬ ፍላጎታቸዉን ለማርካት በሚፈልጉት የእቃ አይነት ወይም ሃገር ቀላልና ፈጣን በሆነ ሁኔታ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

ይህንን ለማድረግ የአትክልትና ፍራፍሬዉን ዋነኛ ስምና የተላከበትን ሃገር ወይም ቦታ ይሞላሉ፡በመቀጠልም የሚከተለዉን መረጃ ያገኛሉ፤

- " 0 ዉጤት ተገኝትዋል " ካለ የመረጡት የአትክልት ወይንም የፍራፍሬ አይነት ወደ አሜሪካ እንዲገባ አልተፈቀደም።
- "# ዉጤት ተገኝትዋል " (ከእቃው አይነትና ሃገር ቀድሞ ይታያል) ካለ እባክዎን CIR የሚለዉን ቁልፍ በመጫን ስለእቃዉ አንዳንድ መረጃዎች ያንብቡ።
    - የቁጥጥሩ ዉሉ "አንድ እቃ ብቻ ለፍተሻ "የሚል ከሆነ ወደ አሜሪካ እንዲገባ ተፈቅድዋል።
    - የቁጥጥሩ ዉሉ "የገባዉ እቃ ምርመራ ላይ ነዉ" ካለ የገባዉ እቃ ለተጨማሪ ምርመራ ወደቡ ላይ ይቆሉ ማለት ነዉ።

ከዚህም በተጨማሪ APHIS ወደ አሜሪካን ሃገር የሚገቡ እፅዋትና የአፅዋት ዉጤቶችን ይቆጣጠራል።ከነዚህም መካከል የሚተከሉ ዕፅዋት (የተለያዩ የዘር አይነቶችና ሸቀጦች) ፤የግብርና ዉጤቶች (እንጨት ጥጥና አበባ) ከተክሎች የሚሰሩ የዕደጥበብ ዉጤቶች (ለምሳሌ ቅርጫት) በልዩ ሁኔታ ጥበቃ የሚደረግላቸዉ ተክሎችና ግብዐቶች (ትላልቅ ደማቅ አበቦች) እንዲሁም ሊጠፉ የተቃረቡ ብርቅዬ የእፅዋት ዘሮች ናቸዉ።

ዉጪ ሃገር የሚገኙ የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እፅዋትና የእፅዋት ዘሮችን ወደ አሜሪካ ለማስገባት አስመጪዉ አካል የግብርና ዉጤቶች ማስገቢያ ፈቃድ ከ APHIS መቀበልና ከተላከበት ሃገር የፎቶሳኒታሪ ሰርተፍኬት ማግኘት ይጠበቅበታል።ፎቶሳኒታሪ ሰርተፍኬት የሚያመለክተዉ የሚገቡት የአቅርቦት ዉጤቶች በሙሉ በተላኩበት ሃገር ህጋዊ ባለሙያዎች ተመርምረዉ ከበሽታና ተባይ የፀዱ መሆናቸዉን ያረጋግጣል።እንዲሁም ሰርተፍኬቱ የዕፅዋቱን የሳይንሳዊ ስም በመጠቀም አሜሪካንን የጉዞና የገቢ ህጎች በሙሉ መሙዋላታቸዉን ይጠቁማሉ።

በአሜሪካ ያላችሁ አስመጪዎች ለሚያስመጡዋቸዉ እቃዎች የግብርና ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል።እርስዎም ፈቃድ ለማዉጣት ከፈለጉ ዕባክዎን APHISን በሚከተሉት አድራሻዎች በመጠቀም የግኙን

USDA-APHIS, የተክሎች መጠበቂያና ማቆያ ጣቢያ
የፈቃድ ማዉጫ ዩኒት
4700 River Road, Unit 133
Riverdale, MD 20737
ስልክ: (877) 770-5990 or (301) 851-2046
ኢሜል: permits@aphis.usda.gov
www.aphis.usda.gov/plant_health/permits/index.shtml

## ስጋ የስጋ ምርቶችና የቁም ከብቶች

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተደጋጋሚ ጊዜ በከብቶች በሽታ ተጋላጭ ከሆኑ ሃገሮች ወደ አሜሪካ የሚገቡ ስጋና የስጋ ዉጤቶች (የተዘጋጁ ምግቦችና የስጋ ምርቶች)፤ዶሮ፤ወተትና የወተት ዉጤቶች (ቅቤና አይብን አያካትትም) እንዲሁም እንቁላል ለማስገባት ካሰቡ ከእንስሳት ህክምና ፈቃድ ሊያስፈልግዎት ይችላል።ሌሎች የምግብ አይነቶች ሆነዉ ጥቂት የስጋ፤የዶሮና የእንቁላለል መጠን ከያዙ ፈቃድ ሊያስፈልጋቸዉ ይችላል።በተጨማሪም የUSDA የምግብ ደህንነትና ፍተሻ ሰርቪስ (FSIS) ወደ አሜሪካ የሚገቡ የስጋ የዶሮና የእንቁላል አቅርቦቶችን ይቆጣጠራል።እነዚህ ምግቦች ወደአሜሪካ ሲገቡ የ APHIS ጤና ማረጋገጫና የ FSIS ህብረተሰባዊ ጤና ማረጋገጫ ማሙዋላታቸዉ ይረጋገጣል።

አስመጪዎች ማስመጣት የተፈቀደባቸዉን ሃገሮችና የእቃ አይነቶች በሚከተለዉ ድህረገፅ ማግኘት ይችላሉ። www.fsis.usda.gov/pdf/Countries_ Products_Eligible_for_Export.pdf.

ወደአሜሪካ የሚገቡ እንስሶችና የእንስሳት ዉጤቶችን የሚፈቅዱ ቅድመሁኔታዎችንና ደንቦችን ለማየት ከፈለጉ  እባክዎን ወደ APHIS የእንስሳት አገልግሎት ድህረገፅን በ www.aphis.usda.gov/import_export/animals/animal_import/animal_imports.shtml.ይጎብኙ

በተጨማሪም አስመጪዎች የ APHISን አስመጪና ላኪ ዋናዉ መስሪያ ቤት በማከተለዉ አድራሻ ሊያገኙ ይችላሉ

USDA-APHIS-NCIE
4700 River Road, Unit 39
Riverdale, MD 20737
ስልክ: (301) 851-3300, option 5
ፋክስ: (301) 734-8226
ኢሜል: AskNCIE.Products@aphis.usda.gov

ይህ በእንዲህ አንዳለ APHIS ወደአሜሪካ የሚገቡ የተለያዩ የከብት ዝርያዎችንና የቤት እንስሶችን (በሬ፡አሳማ፡በግ፡ፍየል፡ፈረስ እና ዶሮ) እንዲሁም ሌሎች የእንስሳት ዝርያዎችን ይቆጣጠራል።የ USDA የአስመጪነት ፈቃድ ለነዚህ እንስሶች ሊያስፈልግ ይችላል፤በተጨማሪም ወደአሜሪካም የሚገቡም ሆነ በአሜሪካ አድርገዉ ወደሌላ ሃገር የሚገቡ የ APHIS ቁጥጥር ስር የነበሩ እንስሶች የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲኖራቸዉ ይጠበቅባቸዋል። ለአንዳንድ የእንስሳ ዘሮችም ልዩ የሆነ መግቢያ ወይም ድህረ መግቢያ የሆነ የእንስሳ ማቆያ ስፍራ ያስፈልጋቸዋል።

በተጨማሪም ወደአሜሪካም የሚገቡም ሆነ በአሜሪካ አድርገዉ ወደሌላ ሃገር የሚገቡ የ APHIS ቁጥጥር ስር የነበሩ እንስሶች የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲኖራቸዉ ይጠበቅባቸዋል።ለአንዳንድ የእንስሳ ዘሮችም ልዩ የሆነ መግቢያ ወይም ድህረ መግቢያ የሆነ  የእንስሳ ማቆያ ስፍራ ያስፈልጋቸዋል።

## የኢፐርሚት ሲስተም

APHIS ከዚህ በፊት ከሚሰራቸዉ ስራዎች በተጨማሪ የኢፐርሚት ሲስተም አገልግሎትን የሚሰጥ ሲሆን በዌብሳት የታገዘ አገልግሎት ለአስመጪዎች በመስጠት ፈቃድ ማረጋገጫና ኡን ያለበትን ሁኔታ በኢንተርኔት እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፤ስለሆነም  ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ሲፈጅ የነበረዉን የፈቃድና የሌሎች ጉዳዩች ማመልከቻ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ረድተዋል። እንዴት ፈቃድ ለማግኘት እንደሚመለከቱ ለማወቅ ለማወቅ ከፈለጉ እባክዎን በድህረገፅ www.aphis.usda.gov/permits/learn_epermits.shtml ይመልከቱ  ኢፐርሚት ሲስተም መመዝገብ ከፈለጉ www.aphis.usda.gov/permits/eauth_epermits.shtml.በመግባት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ

(ለአስመጪዎች ማስታወሻ፤አንዳንድ የገቢ እቃዎች የከተማ ፈቃድ ወይንም የገበሬዎች፡የአሳ ልማት፤የዱር እንስሳትና የአካባቢ ተንከባካቢ ባሉት ማህበራት መሰረት ፈቃድ ሊጠየቅባቸዉ ይችላል)

## ሕገወጥ ግብርናና የንግድ ማህበራት ስምምነት

በአሜሪካ በየአመቱ ቀረጥ ያልተከፈለባቸዉና ህገወጥ የሆኑ የግብርና ዉጤቶች በከፍተኛ ደረጃ እየጨመሩ ይገኛሉ።ይህንን ችግር ለመፍራት APHIS ህገወጥ የሆኑ በሃገሪቱ ተሰራጭተዉ የሚገኙ ግብርና ነክ አቅርቦቶችን ለመለየት ጥረት አደረገ ይገኛል ምክንያቱም እነዚህ ህገወጥ የግብርና ግብአቶች የተለያዩ የእንስሳትና የእፅዋት ተባዩችንና ወረርሽኝ ሊያስከትሉ የሚችሉ በሽታዎችን ተሸክመዉ የአሜሪካንን ጤናማ የእህል የከብቶችንና ሰላማዊ አካባቢዎችን ሊጎዱ ይችላሉ።

የ APHIS ሰራተኞች በሃገሪቱ ዉስጥ የሚገኙ ገበያዎችንና የግሮሰሪ ማስቀመጫ ስፍራዎችን በመመርመርና የሃገር ዉስጥ የኢንተርኔት ንግዶችን በማሰስ ህገወጥ የሆኑ የግብርና እቃዎችን ያጋልጣሉ።እነዚህ እቃዎች ከተገኙ APHIS በፍጥነት በቁጥጥር ስር በማዋል በዚህ ስራ ላይ የነበሩትን ሰዎች አስፈላጊዉን ህጋዊ ቅጣት እንዲቀጡ ያደርጋል።

ስለሆነም ማንኛዉም አስመጪም ሆነ የገበያዉ አካል ተጠቃሚ ህጋዊ የሆነ የግብርና አቅርቦቶችን ብቻ እንዲገዙ ይመከራል።በተጨማሪም ከግብርና እቃዎች ጋር የተያያዙ ሰነዶችና የግብይት መረጃዎች ትክክለኛና ህጋዊ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ሻጮች ስለሚሸጡት እቃ አስፈላጊዉ መረጃ ባይኖራቸዉ APHIS ድህረገፅ ላይ አስፈላጊዉን  ፌዴራላውዊ የቁጥጥር መረጃዎች በመስጠትና ህገወጥ የሆኑ መንገዶችን በማሳየት ሊረዳዎ ይችላል።

የገበያዉ ሃላፊዎችና ባለቤቶች ማንኛዉንም አይነት ህገወጥና ቀረጥ ያልተከፈለበት የግብርና አቅርቦት ካዩ ወይም ከጠረጠሩ በሚከተለዉ የ APHIS አድራሻዎች ሪፖርት ማርረግ ይችላሉ፤ ስልክ፡ (800) 877-3835 ድህረገፅ፡ www.aphis.usda.gov/international_safeguarding.

USDA የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን አቅራቢና ቀጣሪ ነዉ